MedStar Health

# የግለ-ጉዳይ ተግባራት ማስገንዘቢያ

*የሚጸናበት ቀን፣ ኦክቶበር 1, 2009*

ይህ ማስታወቂያ፣ እርሰዎን የሚመለከት የህክምና መረጃ እንዴት ለሌሎች ሊገለጥ እንደሚችልና እርስዎም ቢሆኑ ይህን መረጃ እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ይገልጻል፡፡ እባክዎ በጥንቃቄ ይመልከቱት፡፡

## እኛ ለርስዎ ያለብን ግዴታ/ተጠያቂነት

የህክምና/የጤና መረጃዎ በግለ-ጉዳይነት ይጠበቅ ዘንድ፣ የ"ታካሚ ይቅደም" መሪ ቃላችን ዓቢይ አካል አድርገን እናከብረዋለን፡፡ ለሰዎች ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ እና የጤና አጠባበቅ እድገትኝ ታካሚዎቻችንን የማገልገል ተልዕኮአችንን ወደፊት በማግራመድ መሪ ታዓማኒዎች ለመሆን፣ የታካሚዎችን መረጃ በግለለ-ጉዳይነት መጠበቅን የራዕያችን አቢይ አካል አድርገን እንመለከተዋለን፡፡ በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ለተገለጹ ጉዳዮች ፍጆታ ሲባል፣ ከህክምና መረጃዎችዎ ውስጥ በጣም ጥቂቱን ብቻ ለመጠቀም ጥረት እናደርጋለን፡፡

ጥራት ያለው አገልግሎት እንድናቀርብልዎትና አንዳንድ ህጋዊ ግዴታዎችንም ለማክበር ስንል፣ መርጃዎችን ከርስዎ እንሰበስባለን፣ እናም እንጠቀምባቸዋለን፡፡ የጤና መረጃዎን የግል ምስጢርነት እንድንጠብቅ፣ እንደዚሁም ስለህጋዊ ግዴታ፣ ስለ-ገለ ጉዳይ አጠባበቅ ተግባራችንና፣ ስለርስዎ መብት የሚመለከተውን ይህን ማስታወቂያ እንድንሰጥዎት ህግ ያስገድደናል፡፡ በጣም የቅርብ ወቅት የእሰራር ማስታወቂያዎቻችንን እንድንከተል እንገደዳለን፡፡ አገልግሎታችንን ለሚያከናውኑልን ሌሎች ሰዎችና ድርጅቶች መረጃዎችን አሳልፈን ስንሰጥ፣ የመረጃዎን ግለ-ጉዳይነት እንዲጠብቁ እናስገድዳቸዋለን፡፡ ለመረጃ ግለ-ጉዳያዊ ምስጢርነት ተጨማሪ ከለላ/ጥበቃ የሚሰጡ ሌሎች የምንከተላቸው፣ ለምሳሌም ከአዕምሮ ጤና ጋር የተያያዙ ህጎች፣ የአልኮል መጠጥንና አደንዛዥ ዕጽን የመሳሰሉ ነገሮች አጉል አጠቃቀምንና ተላላፊ በሽታዎችን ወይም ሌሎች የጤና ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ሆነችም አሉ፡፡

ይህ ማስታወቂያ፣ የሚከተሉትን ቦታዎችና ሰዎች ያጠቃልላል፡ በጤና ሰሌዳዎ ውስጥ የጤና መረጃን ለመመዝገብ ኃላፊነት የተሰጣቸው የጤና ባለሙያዎችን ሁሉ፣ እዚህ በሚቆዩበት ጊዜ እርዳታ እንዲያደርጉልዎት ኃላፊነት የተሰጣቸውን የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች ሁሉ፣ ተባባሪዎቻችንና በምድብ ቦታ የሚሰሩ ኮንራተኞቻችን ሁሉ፣ የሆስፒታሉን ልዩልዩ ክፍሎችና ንዑስ ክፍሎች ሁሉ፣ የጤና ተማሪዎችን ሁሉ፣ በሜድስታር የጤና ስርዓት ውስጥ የሚካተቱ የጤና አገልግሎት መስጫ ድርግቶችንና የጤና ግልጋሎቱን የሚያቀርቡትን ሁሉ፣ እንደዚሁም የርስዎን የግል ዶክተርና ሌሎች በዚህ ድርጂት ውስጥ በማገልገል ላይ እንዳሉ ክብካቤውን የሚያቀርቡልዎትን ሰራተኞች ሁሉ፡፡ የግል ዶክተርዎ፣ በግል ቢሮው/ቢሮዋ ወይም በግል ክሊኒኩ/ክሊኒኳ ውስጥ የተሰናዳ የተለዬ የጤና/ህክምና መረጃን የሚመለከት ፖሊሲ ወይም ማስታወቂያ ሊኖረው/ሊኖራት ይችላል፡፡

## የጤና መረጃን እንዴት እንደምንጠቀምና ለሌሎችስ እንዴት አሳልፈን እንደምንገልጥ


© 2009 MedStar Health, Inc.

ህክምና፡ ህክምና ወይም አገልግሎት ለማቅረብ፣ የጤና አጠባብቅዎን ለማስተባበርና ለማቀናጀት፣ ወይም ለህክምናዊ ምርመራና ወደሌላ አገልግሎት ለማሰተላለፍ ሲባል የጤና መረጃዎን ልንጠቀምና ለሌሎች አሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን። በዶክተሮች፣ በነርሶች፣ በቴክኒክ ባለሙያዎች፣ በጤና ተማሪዎችና ሌሎች በዚህ ድርጂት ውስጥ እርስዎን በመንከባከብ ስራ የሚሳተፉ ሰራተኞች፣ ወይም በዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ስራ ውስጥ የሚሳተፉ ከድርጂታችን ውጪ በሆኑ ሰራተኞች መሀከል የጤና መረጃዎን ለመጠቀምና ልንለዋወጥ እንችላለን። የሚያስፈልጉዎትን የተለያዩ አገልግሎቶች፣ ለምሳሌም፣ የመድኃኒት ማዘዣዎችን፣ የላቦራቶሪ ስራዎችንና ራጅ፣ የመሳሰሉትን ለማስተባበር፣ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምና ልንጋራ እንችላለን። እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ፣ ከዚህ ከወጡ በኋላ ለርስዎ ክብካቤን በማቅረብ ስራ ላይ ለሚሳተፉ ከድርጅታችን ውጪ ለሆኑ፣ ለምሳሌም ለቤተሰብ አባላት፣ በቤት ውስጥ የጤና አጠባበቅ አገልግለት ለሚያቀርቡ ድርጅቶች፣ ለቴራፒ/ህክምና ሰጪዎች፣ ለማገገሚያ/የጡረታ ቤቶች፣ ለካህናት/ሼኮችና ለሌሎች እሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን። ወደሌላ አገልግሎት የማስተላለፍን ወይም ምርመራን ለማመቻቸት መረጃን ለጤና ዕቅድዎ ልንሰጥ እንችላለን።

ክፍያ፡ ላቀረብንልዎት ህክምና እና አገልግሎቶች ክፍያችንን እናገኝ ዘንድ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምና አሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን። ይህን መረጃ ከኢንሹራንስ ድርጅትዎ ወይም ይህን የክፍያ ሁኔታ ከሚያስተናብር ሶስተኛ አካል ጋር ልንጋራ/ልናካፍል እንችላለን። ለጤና አጠባበቅ ጉዳይዎ በቀጥታ ከኪስዎ አውጥተው ሙሉውን ክፍያ እርስዎ የሚከፍሉ ከሆነ፣ መረጃዎን ለኢንሹራንስ ድርጅትዎ እንዳናካፍል ሊጠይቁን ይችላሉ። ለምን ዓይነት ጥቅሞች ብቁ እንደሆኑ ለማረጋገጥ፣ ቅድመ ማረጋገጫ ለማግኘት፣ እና ለሚደርግልዎት የጤና ክብካቤ የሚክፍሉን መሆናቸውን ለማረጋገጥ ስንል የኢንሹራንስ ድርጅትዎን ልንጠይቅ እንችላለን። ለክፍያ ኃላፊነትን ለሚወስዱ ሶስተኛ አካላት፣ ለምሳሌም ለብቤተሰብ አባላት፣ እለዚያም እርስዎን እናስከፍል እንደሆነ፣ መረጃውን እሳልፈን እንገልጣለን። ክፍያዎችን በማስተናበር ለሚረዱን ሶስተኛ አካላት፣ ማለትም ለክፍያ አስተናባሪ ድርጅቶች፣ የይገባኛል ጥያቄን ለሚያስተናብሩ ድርጅቶች፣ እና ለዕዳ ሰብሳቢ ድርጅቶች መረጃውን አሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን።

የጤና ጥበቃ አሰራሮች፡ ድርጅታን የስራ ተግባሩን በአግባቡ ለማከናወን እንዲችልና ታካሚዎቻችን ሁሉ ጥራት ያለው ክብካቤ እንደሚያገኙ ለማረጋገጥ፣ የጤና መረጃዎን ለመጠቀምና አሳልፈንም ለመግለጥ እንችላለን። ያገኟቸውን አገልግሎቶች ጥራት፣ ወይም ለርሰዎ ክብካቤ ሲያቀርቡ የነበሩ ሰራተኞቻችንን የስራ ክንዋኔ ለመገምገም፣ የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። አሰራራችንን ለማሻሻል ወይም የተሻለ ክብካቤ ለማቅረብ የሚያስችሉ መገዶችን ለመፈለግ የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። ለህክምና ባልደረቦች እድል ወይም መብት ለመስጠት ወይም የጤና ባልደረቦቻችንን የአሰራር ብቃት ለመገምገም የጤና መረጃን ልንጠቀም እንችላለን። ምን ዓይነት ተጨማሪ አገልግሎት ማቅረብ እንደሚገባንና ምናልባትም አዳዲስ ህክምናዎች የበለጠ ውጤታማ ይሆኑ እንደሆነ ለመወሰን የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እንችላለን። ለግምገማና ለትምህርት ዓላማዎች መረጃን ለተማሪዎችና ለባለሙያዎች ልንገልጥ እንችላለን። አሰራራችን እንዴት እንደሆነ ለማወዳደርና የት ቦታ ላይ ማሻሻል እንደሚገባን ለማየት በጃችን የሚገኝ የጤና መረጃን ከሌሎች የጤና ድርጅቶች የጤና መረጃ ጋር አቀላቅለን ልንጠቀም እንችላለን። ህግን አክብረን እየሰራን ስለመሆናችን

 © 2009 MedStar Health, Inc.

እርግጠኞች ለመሆን፣ ለስራ ዕቅድ ዓላማ መረጃን ልንጠቀም እንችላለን፣ ወይም ለጠበቆች፣ ለሂሳብ አያያዝ ባለሙያዎች (ለአካውንታንቶች)፣ ለአማካሪዎች እና ለሌሎች መረጃውን ልንገልጥ እንችላለን:: ማንነትን ገላጭነቱ የተደበቀ መረጃን በመጠቀም፣ ሌሎች ወገኖች የርስዎን ማንነት ሳያውቁ ስለጤና አጠባበቅና የጤና አጠባበቅ አቅርቦቶች ለማጥናት ይችሉ ዘንድ እርሰዎንትዎን የሚገልጠውን የጤና መረጃን ክፍል ልናስወጣው እንችላለ::

**የጤና መረጃን ስለመ'ለዋወጥ:** ለህክምናዎ፣ ለክፍያ፣ ወይም ለሌሎች የጤና አጠባበቅ የስራ ጉዳዮች አገልግሎት ሲባል፣ በበርካታ የጤና ግልጋሎት አቅራቢዎች ወይም ሌሎች የጤና አካላት መሀከል የሚደረገውን ጥ'ብቅ ኤሌክትሮኒካዊ የጤና መረጃዎን ልውውጥ ለማመቻቸት፣ በጤና መረጃ ልውውጥ ውስጥ እንሳተፋለን:: ይህ ማለት፣ እያንዳንዳችን በየበኩላችን የተሻለ አገልግሎት ለማቅረብና የጤና ህክምናዎን በጥሩ ሁኔታ ለማቀነባበር እንችል ዘንድ፣ በእጃችን ያለውን ወይም የሰበሰብነውን እርስዎን የሚመለከት መረጃ፣ ለውጪ አካላት፣ (ለምሳሌም፣ ለስፒታሎች፣ ለዶክተሮች ቢሮዎች፣ ለመድኃኒት ቤቶች፣ ወይም ለኢንሹራንስ ድርጅቶች)፣ ልናካፍል እንችላለን፣ ወይም ከነዚህ አካላት እርሰዎን በሚመለከት በእጃቸው ያለውን ወይም ያሰባሰቡትን እርሰዎን የሚመለከት መረጃ (ለምሳሌም፣ የመድኃኒት ህክምና ታሪክዎን፣ የአጠቃላይ ህክምና ታሪክዎን፣ ወይም የኢንሹራንስ መረጃ) ልንቀበል እንችላለን:: በተጨማሪም፣ ማንኛውንም የሜድስታር የጤና ድርጅት ከጎበኙ፣ የጤና መረጃዎ፣ እርስዎን ለሚንከባበከቡ፣ የጤና ግልጋሎትዎን ለሚያስተባብሩ፣ ወይም ለሌላ የተፈቀደ አገልግሎት መረጃውን ለሚጠቀሙ ለሌሎች የክሊኒክ ባልሙያዎችና የክሊኒክ ባልደረቦች ግልጽና ዝግጁ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል::'

**የቀጠሮ ማንቂያዎችና የአገልግሎት መረጃ:** ቀጠሮዎን እንዲያስታውሱ ለማንቃት፣ ወይም ምናልባትም እርሰዎ የሚፈልጓቸውን የህክምና አማራጮችን ወይም ሌሎች ጤና-ነክ አገልግሎቶችን ወይም ጥቅሞችን ለርስዎ ለማሳወቅ፣ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም ልናጋልጥ እንችላለን::

**በርሰዎ ክብካቤ ውስጥ የሚሳተፉ ግለሰቦች፣** እርሰዎ አይሆንም ካላሉን በስተቀር፣ የጤና መረጃዎን፣ በርስዎ ክብካቤ ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች፣ ለምሳሌም፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ጓደኞች ልንሰጥ እንችላለን:: ለጤና ጉዳይዎ በመክፈል ለሚረዳዎት ሰው መረጃዎን ልንሰጥ እንችላለን:: መረጃዎን ለሌሎች የጤና አጠባበቅ ባልሙያዎች፣ የመንግስት ተወካዮች፣ ወይም በአስቸኳይ ወይም በአደጋ ወቅት፣ ቤተስብዎን ወይም ጓደኞችዎን ለመገናኘት፣ ወይም የአደጋ ወቅት እርዳታን ለማስተባበር ይችሉ ዘንድ፣ የጤና መረጃዎን ለአደጋ ጊዜ እርዳታ አቅራቢ ድርጅቶች፣ ለምሳሌም እንደ ቀይ መስቀል ለመሳሰሉ የእስቸኳይ ጊዜ እርዳት አቅራቢ ድርጅቶች ልንሰጥ እንችላለ::

**የታካሚ የስም ማውጫ:** እርስዎን በስምዎ ጠርቶ ለሚጠይቀን ሰው ለመስጠት፣ ስምዎን፣ በድርጅቱ ውስጥ ያሉበትን ቦታ፣ እና አጠቃላይ ሁኔታዎን በማውጫ ሰሌዳ ውስጥ መዝግበን እናስቀምጣለ:: ምንም እንኳን ስምዎን የማያውቁ ቢሆኑም፣ ይህን መረጃዎንና ሀይማኖታዊ ሁኔታዎን ለካህናት/ሼኮች እንሰጣለን:: ስምዎን ከስም ማውጫ ሰሌዳችን ውስጥ እንድሰርዝ ሊጠይቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን፣ ይህን ካደርጉ ጠያቂዎችዎና ስጦታ የሚያመጡልዎት ሰዎች እርሰዎ የትኛው ክፍል ውስጥ እንደሆኑ ሊያውቁ አይችሉም:: ስምዎን ከስም ማውጫ ሰሌዳው ውጪ ሆኖ


© 2009 MedStar Health, Inc.

እንዲቆይ ቢጠይቁም እንኳን፤ አስቸኳ የአደጋ ጊዜ አዋጅ በታወጀበት ሁኔታ ወቅት፤ ለአደጋ እርዳታ ጥረት አገግሎት፤ መረጃዎን ልናካፍል እንችላለን።

**ገንዘብ የማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች፡** የጤና አጠባበቅ ተልዕኮአችን በአብዛሃኛው በግል የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ የተመሰረተ ነው። ለገንዘብ ማሰባሰብ ፕሮግራሞቻችን ዕርዳት ለመለገስ እንዲችሉ ዕድሉን እንስጥዎት ዘንድ ግንኙነት እንዲናደርግልዎት፤ የጤና ግልጋሎት ያገኙባቸውን ቀናት ጨምሮ፤ ነገር ግን የህክምና መረጃን ሳይጨምር፤ ስምዎንና ሌሎች ውሱን መረጃዎችን ልንጠቀም እንችላለን። ለገንዘብ ማሰባሰብ ጉዳዮች ግንኙነት ካደርግንልዎትና፤ ነገርግን ግን ወደፊት ግንኙነቱን እንዳናደርግልዎት ከፈለጉ እንዴት ሊጠይቁን እንደሚችሉ ይነገርዎታል

**ምርምር፡** አንድን የምርምር ሃሳብ በመገምገምና የርስዎን የጤና መረጃም በግለ-ጉዳይነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስነስርዓቶችን በአግባቡ በማስቀመጥ ምርምሩን ባጸደቀውና ከኦፌሴላዊ የምርምር ግምገማ ቦርዳችን በአንዱ እውቅና ለተሰጠው የምርምር ስራ፤ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም አሳልፈን ልንገጥ እንችላለን። የምርምር ፕሮገሬ/እቅድ ለማካሄድ በማዘጋጀት ላይ ለሆነ ተመራማሪ፤ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም አሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን።

**የሰውነት አካል ክፍልንና የአካል ቁራጭን ስለመለገስ፡** የሰውነት አካል ክፍልን ከመለገስ፤ ዓይንን ወይም ሌላ የሰውነት አካል ቁራጭን ለሌላ ከማስተላለፍ፤ ወይም ከሰውነት አካል ልገሳ ባንክ ጋር በተያያዘ፤ እነዚህን ድርጊቶች ለማስተባበርና ለማቀናጀት የጤና መረጃዎን ልንጠቀም ወይም አሳልፈን ልንገልጥ እንችላለን።

**የህዝብ ጤና እንቅስቃሴዎች፡** ኦፊሴላዊ ተግባራቸው፡ በሽታን፤ ጉዳትን፤ ወይም አካለ-ስንኩልነትን መከላከልና በመቆጣጠርን የሚያካትት ለሆኑት ለህዝብ ጤና ወይም የህግ ባለስልጣናት፤ የጤና መረጃዎን ልናጋልጥ እንችላለን። ለምሳሌ፤ ውልደትን፤ ሞትን፤ እና የተለያዩ በሽታዎችን የሚመለከቱ አንዳንድ መረጃዎችን፤ ለመንግስት አካላት ሪፖርት ልናደርግ እንችላለን። ተግባራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ በህግ ለተፈቀደላቸው ለአስከሬን ምርመራ ባለሙያዎች፤ ለጤና መርማሪዎች፤ እና ለቀብር ስነስርዓት አስተናባሪ ዲሬክተሮች፤ የጤና መረጃን ልንገልጥ እንችላለን። በሚ'ወሰዱ ድኃኒቶች ሳቢያ የሚከሰቱ አሉታዊ ውጤቶችን፤ በአንዳንድ የፍጆታ ነገሮች ሳቢያ የሚከሰቱ ችግሮችን ሪፖርት ለማድረግ፤ ወይም ሰዎች እየተጠቀሙባቸው ያሉትን ነገሮች እንዲመልሱ/መጠቀማቸውን እንዲያቆሙ ለማሳወቅ፤ የጤና መረጃን ልንጠቀም ወይም ልናጋልጥ እንችላለን። አንድ ሰው ለሆነ በሺታ ተጋልጦ እንደሆነ ወይም በበሺታ የመያዝ ወይም በሺታን የመበተን አደጋ ውስጥ እንደሆነ ሰውየውን ለማሳወቅ፤ የጤና መረጃን ልንጠቀም ወይም ልናጋልጥ እንችላለን።

**ብርቱ ስጋት ለጤንነትና ደህንነት፡** በርስዎ፤ በህዝብ፤ ወይም በሌላ ሰው ላይ የተጋረጠ ብርቱ የጤና እና የደህንነት ስጋት ሲኖር፤ ስጋቱን መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የጤና መረጃዎን ልንጠቀምና ልናጋልጥ እንችላለን። የጤና መረጃውን የምንገልጠው ሁኔታውን ለመከላከል ወይም ስጋቱን ለመቀነስ ተመጣጣኝ ብቃት ላለው ሰው፤ ለምሳሌም ለህግ አርከባሪ ወይም ለመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ነው።


© 2009 MedStar Health, Inc.

በህግ፣ በህጋዊ አሰራር ሂደቶች፣ በጤና ቁጥጥር እንቅስቃሴዎች እና በህግ አስከባሪዎች የተጣለ ግዴታ፡ በፌዴራል፣ በስቴትና በሌላ ህግ መተጠየቅን ጊዜ፣ የጤና መረጃዎን ልንገልጥ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ የጥቃት ሰለባዎችን፣ በግዴለሽነት የደረሱ ችግሮችን ወይም የቤት ውስጥ ረብሻን፣ እንደዚሁም በጥይት ወይም በሌላ ምክንያት የቆሰሉ በሽተኞችን ሪፖርት እንድናደርግ እንገደድ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ እንደ ፍርድ ቤት መጥሪያ፣ የግኝት ጥያቄ፣ የፍርድ ቤት ማዘዣ፣ መጥሪያ፣ ወይም ሌሎች ህጋዊ ሂደቶችን በሚመለከቱ ህጋዊና አስተዳደራዊ የፍትህ ስርዓታዊ ሂደቶች ስንታዘዝ የጤና መረጃዎን ልንገልጥ እንችላለን፡፡ ተጠርጣሪዎችን፣ ኮብላዮችን፣ ምስክሮችን፣ የወንጀል ሰለባዎችን፣ ወይም የጠፉ ሰዎችን ለመለየትና የትነታቸውን ለመከታተል ሲባል፣ የጤና መረጃን ለህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ልንገልጥ እንችላለን፡፡ በድርጅታችን ክልል ውስጥ የደረሰ የሞት አደጋ የተከሰተው በወንጀል ተግባር ሊሆን ይችላል፣ ወይም በድርጅታችን ክልል ውስት በደረሰ የወንጀል ድርጊት ሊሆን ይችላል ብለን ስናምን፣ የጤና መረጃን ለህግ አስከባሪ ባለስልጣናት ልንገጥ እንችላለን፡፡ በህግ ለተፈቀደላቸው/እውቅና ለተሰጣቸው እንቅስቃሴዎች፣ ለምሳሌም እንደ ኦድት/የሂሳብ ምርመራ፣ ምርመራዎች፣ ቁጥጥርና ፈቃድን ለመሳሰሉት፣ የጤና መረጃን ለጤና ቁጥጥር ድርጅቶች ልንገልጥ እንችላለን፡፡

**ለየት ያሉ የመንግስት ስራዎች፡** ወታደር ወይም ከጦርነት ዘመቻ ተመላሽ ከሆኑ፣ በዕዝ ባለስልጣናት ስንታዘዝና ስንጠየቅ፣ የጤና መረጃዎን እንሰጣለን፡፡ ለብሄራዊ ደህንነት ጉይ፣ ለምሳሌም፣ የዩናይተድ ስቴትስ ፕሬዚደንትን ደህንነት ለመጠብቅ ወይም ለህጋዊ የደህንነት እንቅስቃሴ ተግባራት የጤና መረጃን ህጋዊ እውቅና ላላቸው የፌዴራል ባለስልጣንት እንሰጣለን፡፡ ለውጭ አገልግሎት የህክምና ተስማሚነት ውሳኔ ለማድረግ፣ የጤና መረጃን አጋልጠን ልንሰጥ እንችላለን፡፡

**የጠባይ ማረሚያ ቤቶች፡** በጠባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ከሆኑ ወይም በህግ አስከባሪ ባለስልጣን ጥበቃና ቁጥጥር ስር ከሆኑ፣ የጤና መረጃዎን ለጠባይ ማረሚያ ተቋሙ ወይም ለህግ አስከባሪ ባልስልጣኑ አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን፡፡ ለርስዎ ጤንነትና ደህንነት፣ ለሌሎች ጤንነትና ደህንነት፣ ወይም ለጠባይ ማረሚያው ሰላምና ደህንነት ሲባል የጤና መረጃዎን አሳልፈን ልንሰጥ እንችላለን፡፡

**የሰራተኞች ካሳ፡** ተፈጻሚነት ያለው የሰራተኞች ካሳ እና ተመስሳይ ህግጋት በሚያዙት መሰረት፣ የጤና መረጃዎን ልንገልጥ እንችላለን፡፡

**የርስዎ የጽሁፍ ማረጋገጫ/ፈቃድ፡** በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ያልተካተቱ ሌሎች የርስወዎን የጤና መረጃ አጠቃስቀምና እገላለጥ የሚመለከቱ ሁኔታዎች፣ ወይም እኛን የሚገዙን ሌሎች ህጎች ቢኖሩ፣ እርስዎ በሚሰጡት የጽሁፍ ማረጋገጫ/ፈቃድ ብቻ ነው ሊካተቱ የሚችሉት፡፡ በጽሁፍ ያቀረቡትን ማረጋገጫ ወይም ፈቃድ፣ በማንኛውም ጊዜ በጽሁፍ በማቅረብ ሊሰርዙት ይችላሉ፣ እኛም በጽሁፍ ባቀርቡት ማረጋገጫዎ ስር የነበረውን የጤና መረጃዎን አጠቃቀምና አገላለጥን ለወደፊቱ ከመጠቀም እናቆማለን፡፡ በጽሁፍ አቅርበውት በነበረው ማረጋገጫዎ መስረት ተገልጠው የበሩ መረጃዎችን ግን ወደኋላ ልንመልሳቸው አንችልም፣ እናም ያቀርብንልዎትን የጤና ክብካቤ የሚመለከተውን በሚመለከት የያዝነውን ሪኮርድ ይዘን ለማቆየት እንገደዳለን፡፡

## የጤና መረጃዎን በሚመለከት ለግለ-ጉዳይ አጠባበቅ ያለዎት መብት፡

 © 2009 MedStar Health, Inc.

## የዚህን የግል-ጉዳይ አጠባበቅ ማስታወቂያ ቅጂ የማግኘት መብቶች

የወቅቱን ማስታወቂያችንን ቅጂ በግቢያችንና በድረ-ገጻችን www.medstarhealth.org ላይ እንለጥፋለን። የወቅቱ ማስታወቂያችን ቅጂ በመ'መዝገቢያ አካባቢያችንና በጥያቄ መሰረት ሊገኝ ይችላል። የወቅቱን የግል-ጉዳይ አጠባበቅ ተግባር ማስታወቂያችንን ቅጂ ለማዘዝ፣ (በነጻው ስልካችን) 877-811-3411 ይደውሉልን።

## የጤና ሬኮርድዎን የማየትና ቅጂ የማድረግ መብት

የጤና ሬኮርድዎን ወይም የክፍያ ሬኮርድዎን የመመልከትና ቅጂውን የማግኘት መብት አለዎት። ይህን ለማድረግ፣ ህክምናዎን የተቀበሉበትን ድርጅት ወይም ከታች የተቀመጠውን የግል-ጉዳይ አጠባበቅ ቢሮ ይገናኙ። ጥያቄዎን በጽሁፍ እንዲያደርጉ ይጠየቁ ይሆናል። የጤና ሬኮርድዎን ቅጂ የሚፈልጉ ከሆነ፣ በህግ በተፈቀደው መሰረት ኮፒ የማድረጊያና የመላኪያ ዋጋ እንዲከፍሉ ይጠየቁ ይሆናል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ጥያቄዎን ላናስተናግድ እንችል ይሆናል። ይህን ካደረግን፣ ጥያቄዎን ያልተቀበልንበትን ምክንያታችንን በጽሁፍ እናሳውቀዎታለን፣ እንደዚሁም ያልተቀበልነው ጥያቄዎ እንደገና እንዲታይልዎት የመጠየቅ መብትዎን እናብራራልዎታለን።

## የጤና ሬኮርድዎን የማሻሻል መብት:

ከጤና ሬኮርድዎ ውስጥ አስፈላጊ መረጃ ሳይካተት ቀርቷል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ የተዘለለ መረጃውን በሬኮርድዎ ውስጥ በመጨመር እንድናስተካክለው የመጠየቅ መብት አለዎት። ጥያቄዎ በጽሁፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ የጥያቄዎን ምክንያት የያዘ መሆን አለበት። ጥያቄዎን ለማቅረብም፣ ህክምናዎን ያገኙበትን ድርጅት ወይም ከታች የተመለከተውን የግል-ጉዳይ አጠባበቅ ቢሮ ይገናኙ። እንዲሻሻልልዎት የሚጠይቁት መረጃ በኛ በራሳችን የተፈጠረ/የተመዘገበ ካልሆነ፣ ወይም የያዝነው መረጃ ትክክልና የተሟላ ነው ብለን የምናን ከሆነ፣ ወይም መረጃው እርስዎ እንዲያዩትና ቅጂም እንዲያደርጉ በህግ ከተፈቀደልዎት ኮርድ ውስጥ የተያዘ ካልሆነ፣ ጥያቄዎን ላንቀበል እንችላለን። የማሻሻል ጥያቄዎን ብንቀበለውም እንኳን፣ በሬኮርድዎ ውስጥ ተይዞ ያለውን ማንኛውንም መረጃ ልንሰርዝ አንችልም።

## ለሌሎች የገለጥናቸውን ዝርዝሮች የማግኘት መብት:

ለሌሎች የገለጥናቸውን የጤና መረጃዎችዎን ዝርዝሮች የመጠየቅ መብት አለዎት። ዝርዝሩ፣ ለህክምና ጉዳይ፣ ለክፍያ እና ለጤና አጠባበቅ የስራ ጉዳዮች ከገለጥናቸው በውረቀት ላይ የሰፈሩ ሬኮርዶችን እይዝም። በርስዎ ፈቃድ የተገለጡትን እና አንዳንድ በህግ ተነጥለው የተከለከሉትን የተገለጡ ረኮርዶች አይዝም። ዝርዝሩ፣ ከ ኤፕሪል 14, 2003 በፊት የተገለጡትን አይዝም። ሬኮርድዎ በኤሌክትሮኒካዊ የህክምና ሬኮርዶች ስርዓት ውስጥ የተቀመጠ ከሆነ፣ የተገለጡ መረጃዎች ዝርዝር፣ ለህክምና፣ ለክፍያና ለጤና አጠባበቅ ስራ ጉዳዮች ከጃኒዋሪ 1, 2014 በኋላ ጀምሮ የገለጥናቸውን ሁሉ ያጠቃልላል። ዝርዝሩ ጥያቄዎን ካቀረቡበት ቀን የሶስት ዓመታት ጊዜ ወደኋላ ያሉትን ተገላጮች ብቻ የማጠቃለል ውሱን ገደብ ያለበት ነው። ጥያቄዎ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል። የተገለጡ መረጃዎችን ለመጠየቅ፣ እባክዎ ህክምናዎን ያደረጉበትን ድርጅ፣ ወይም


© 2009 MedStar Health, Inc.

ከታች የተዘረዘረውን የግል-ጉዳይ ቢሮ ይጠይቁ። በ12 ወራት የጊዜ ክልክል ውስጥ የሚጠይቁት የመጀመሪያውን ዝርዝር በነጻ ያገኛሉ። ለተጨማሪ ዝርዝሮች ግን፣ ህጉ በሚያዘው መሰረት ዋጋ እናስከፍላለን።

***አንዳንድ መረጃዎችን የመጠቀም ወይም የመግለጥ ገደብ እንዲደርግ የመጠየቅ መብት:***

የጤና መረጃዎን አጠቃቀማችንና ለሌሎችም የምናደርገው አገላለጣችን ገደብ ይኖርበት ዘንድ ሊጠይቁን ይችላሉ። ላገኙት ነገርና አገልግሎት በሙሉ እራስዎ ከኪስዎ አውጥተው የከፈሉ ከሆነ፣ለክፍያም ሆነ ለጤና አጠባበቅ ስራ ጉዳይ ሲባል፣ የጤና መረጃዎን ለጤና እቅድዎ እንዳንገልጥ የሚከለክሉን የተወሰኑ ጥያቄዎችን እንድናስተናግድ ህግ ያዝብናል። በመረጃ አጠቃቀምና አገላለጥ ላይ ገደብ ለመጣል የሚቀርቡ ከዚህ የተለዩ ሌሎች ጥያቄዎችን እንድንቀበል ግን ህግ አያስገድደንም። ከተቀበልነው ግን፣ አስቸኳይ ህክምና የሚያስፈልግዎት ካልሆነ በስተቀር፣ በጥያቄዎ መሰረት እንሰራለን። ጥያቄዎ በጽሁፍ መቅረብ ይኖርበታል። ጥያቄ ለማቅረብ፣ እባክዎ ህክምናዎን ያደረጉበትን ድርጅ፣ ወይም ከታች የተዘረዘረውን የግል-ጉዳይ ቢሮ ይጠይቁ።

***የጤና መረጃዎን እንዴት ማግኘት እንደሚፈልጉ የመምረጥ መብት:***

በሆነ መንገድ፣ ለምሳሌም፣ በደብዳቤ ወይም በፋክስ፣ ወይም የሆነ ቦታ፣ ማለትም በመኖሪያ ቤት አድራሻ፣ ወይም በፖስታ ሳጥን እንድንገናኝዎት የመጠየቅ መብት አለዎት። በተቻለን መጠን ሁሉ ጥያቄዎን ለማክበር እንሞክራለን። ጥያቄዎ በጽሁፍ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ እንዴት ወይም የት እንደምንገናኝዎት የሚገልጽ መሆን አለበት። ጥያቄ ለማቅረብ፣ እባክዎ ህክምናዎን ያደረጉበትን ድርጅ፣ ወይም ከታች የተዘረዘረውን የግል-ጉዳይ ቢሮ ይጠይቁ።

***<u>የግንኙነት ሰው</u>***

የግል-ጉዳይ አጠባበቅ መብትዎ ተጥሷል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ አቤቱታዎን በጽሁፍ በማድረግ ከታች ለተገለጸው የግንኙነት ሰው ማቅረብ ይችላሉ። ስለግል-ጉዳይ አጠባበቃችን ጉድለት አቤቱታ ቢያቀርቡ፣ ይህን በማድረግዎ የተነሳ ምንም ዓይነት የብቀላ እርምጃ እንወስድም። የአቤቱታ ማመልከቻ ለኛ ወይም ለጤና ጥበቃ ክፍልና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ዋና ጸሀፊ ለማቅረብ ከፈለጉ፣ ከታች የተገለጸውን የግል-ጉዳይ አጠባበቅ ቢሮአችንን ይገናኙ።

ስለዚህ ማስታዎቂያ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወይም የግል-ጉዳይ መብትዎን መጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ ህክምናዎን ያገኙበትን ድርጅት ወይም የግል-ጉዳይ ቢሮአችንን ይገናኙ።


Privacy Officer MedStar Health, Inc.<br>
5565 Sterrett Place Columbia, MD 21044<br>
1- 877- 811- 3411 (በነጻው ስልካችን)<br>
<u>PrivacyOfficer@MedStar.net</u>


***<u>ይህን የግል-ጉዳይ ተግባርራት ማስታወቂያን ስለመቀየር:</u>***

ይህን ማስታወቂያ የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። አሁን በእጃችን

 © 2009 MedStar Health, Inc.

ያለውና እንደዚሁም ወደፊት የምንቀበለው እርስዎን የሚመለከት የጤና መረጃ ሁሉ፣ በዚህ በተሻሻለው ማስታወቂያ ተፈጻሚነት እንዲኖረው የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው።

**El Aviso sobre Prácticas de Privacidad está disponible en español.**

개인 정보 보호 정책 관행의 공지 사항 한글로 사용할 수

있습니다.

**بيان ممارسات الخصوصية متوفر باللغة العربية.**

**通知隐私做法是可以在简体中文。**

**Có sẵn bản tiếng Việt cho Thông Báo Cách Thực Hiện Sự Riêng Tư**

Уведомление о конфиденциальности доступно на русском языке.

*የግርጌ ማስታወሻ፡ በኮሎምቢያ፣ ሜሪላንድ የሚገኘው የሜድስታር የጤና ድርጅት፣ ሰፊውን የባልቲሞር/ዋሽንግተን ክልል የሚያገለግል፣ በማህበረሰባዊ መሰረት ላይ የቆመ፣ አትራፊ-ያልሆነ የጤና ድርጂት ነው። የጤና ስርዓቱ፣ በልቅናቸው የታወቁ በርካታ የጤና አጠባበቅ ግልጋሎት አቅራቢዎችንና ሌሎች የተለያዩ የጤና አጠባበቅ አካላትን ያቀፈ ነው። እነዚህ አካላት ለያንዳንዳቸው በየግላቸው የሚሰሩና የተለያዩ ቀጣሪዎች ያሏቸው ቢሆንም፣ ለጋራ ተልዕኮና ምግባር ይሰራሉ። የሜድስታር ጤና ተልዕኮ፣ ታካሚዎቻችንን፣ እነሱንም የሚንከባከቡ ሰራትኞቻችንንና ማህበረሰባችንን ማገልገል ሲሆን፣ ራዕያችንም ክብካቤን ለሰዎች በማቅርብ ደረጃ መሪ ተዓማኒዎች መሆንና የጤና አጠባበቅን ማሳደግ ነው። ከዚህ ግብ ለመድረስ ስንሰራ፣ እያንዳንዱ የሜድሳትር አካል ድርጅት የየግሉን የግለ-ጉዳይ ምስጢር አጠባበቅ ፖሊሲውን ማጠናከር፣ እና ለሰራተኞች ምግባረ ጥሰት፣ የዲሲፕሊናዊና ሌሎች እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚገባው ነው። እባክዎ ያስታውሱ፣ ለዚህ የግለ-ጉዳይ አጠባበቅ ማስታወቂያ አገልግሎት፣ የሜድስታር አያት ኩባንያ እና ሁሉም ንዑሳን ክፍሎቹ በጥቅል አነጋገር "ሜድስታር ጤና" ተብለው ይገለጻሉ። ለግለ-ጉዳይ አገልግሎት ብቻ ሲባል፣ የሜድስታር ጤና አደርጃጀት፣ በተናጠል ህጋዊ አካልነት ያልቸው ሆነው ነገር ግን በጋራ የዓላማ ቁርኝት የተሳሰሩ የተለያዩ አካላት በአንድ ጃንጥላ ድርጅት ስር ሊሰየሙ ይችላሉ በሚለው በ45 ሂህማ ኸ164.504(ሳ)(1) መሰረት የተዋቀረ ነው።*



© 2009 MedStar Health, Inc.